

AM

“በዱብሊን አሠራር ውስጥ ነኝ -- ይሄ ምን ማለት ነው?”

ለ

መረጃ በዱብሊን አሠራር ውስጥ ለሚገኘው አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች፣ የድንጋጌ (EU) ቁጥር 604/2013 አንቀጽ 4


ይሄ ወረቀት የተሰጠዎት በዚህ አገር ወይም በሌላ የዱብሊን አገር ለአለም አቀፍ ጥበቃ (ጥገኝነት) ጥያቄ ስላቀረቡና እዚህ ያሉት ሰራተኞች ጥያቄዎትን ለመመርመር ሀላፊነቱን የሚወስደው ሌላ አገር ነው ብለው ለማመን ምክንያቶች ስላላቸው ነው።

ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር የምንወስነው በአውሮፓ ሕብረት በተዘጋጀ የ 'ዱብሊን' ድንጋጌ የተሰኘ አሠራር ነው። ይሄ ሂደት 'የዱብሊን አሠራር' ይባላል። ስለዚህ አሠራር ሊኖርዎት የሚችሉትን ተዘውታሪ ጥያቄዎች ይህ ወረቀት ለመመለስ ይሞክራል።

በዚህ ወረቀት ላይ ያልገባዎት ነገር ካለ ሠራተኞቻችንን ይጠይቁ።

ይህ ወረቀት ለመረጃ አገልግሎት ብቻ ይውላል። አላማውም የ ዱብሊን አሠራን አስመልክቶ ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች አስፈላጊ መረጃዎችን መስጠት ነው። በራሱ ሙቢቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም/አያስከትልም። በዱብሊን አሠራር ስር ያሉ መንግስታትና ሰዎች ሙቢቶቹ እና ግዴታዎቹ በድንጋጌው (EU) 604/2013 ውስጥ የተካተቱት ናቸው።

©የአውሮፓ ሕብረት 2014
መልሶ ማተም ይፈቀዳል። እያንዳዱን ፎቶ ለማንኛውም አገልግሎት ለመጠቀምም ሆነ እንደገና ለማተም፣ ከኮፒ ራይቱ ባለቤቶች በቀጥታ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል።



የዱብሊን አገሮች 28ቱን የአውሮፓ ሕብረት አገሮች ያካትታል (ኦስትሪያ (AT), ቤልጂየም (BE), ቡልጋሪያ (BG), ክሮሺያ (HR), ሳይፕረስ (CY), ቼክ ሪፓብሊክ (CZ), ዴንማርክ (DK), ኢስቶኒያ (ET), ፊንላድ (FI), ፈረንሳይ (FR), ጀርመን (DE), ግሪክ (EL), ሀንጋሪ (HU), አየርላድ (IE), ጣሊያን (IT), ላቲቪያ (LV), ሊቱኒያ (LT), ሉክሰምበርግ (LU), ማልታ (MT), ኔዘርላንድስ (NL), ፖላንድ (PL), ፖርቹጋል (PT), ሮማኒያ (RO), ስሎቫኪ (SK), ስሎቬኒያ (SI), ስፔን (ES), ስዊድን (SE), ዩናይትድ ኪንግደም (UK)) እንዲሁም ከዱብሊን ድንጋጌ ጋር “የተቆራኙ” 4 አገሮች (ኖርዌይ (NO), አይስላንድ (IS), ስዊዘርላንድ (CH) እና ሊችቴንስቴይን (LI))

“በዱብሊን አሠራር ውስጥ ያለሁት ለምንድን ነው?”

የዱብሊን ድንጋጌ 32 አገሮችን በሚያካትት የመልክአ ምድራዊ ቀጠና ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ **የ‘ዱብሊን አገሮች’ የሚከተሉት ናቸው፡** ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮሺያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼክ ሪፓብሊክ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሀንጋሪ፣ አየርላድ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቹጋል፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬኒያ፣ ስፔን፣ ስዊድን፣ ዩናይትድ ኪንግደም) እንዲሁም ከዱብሊን ድንጋጌ ጋር “የተቆራኙ” 4 አገሮች (ኖርዌይ፣ አይስላንድ፣ ስዊዘርላንድ እና ሊችቴንስቴይን)

የዱብሊን አሠራር ለጥገኝነት ያቀረቡትን ጥያቄ ለመመርመር የትኛው አገር ሀላፊነቱን እንደሚወስድ ይወስናል፡፡ ይህም ማለት ከዚህ አገር ተነስተው ማመልከቻዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን ወደሚወስድ ሌላ አገር ሊዛወሩ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

የዱብሊን አሠራር ሁለት ፋይዳዎች አሉት፡

- ለጥገኝነት ያቀረቡት ማመልከቻ ማመልከቻዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን በወሰደው አገር ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ጋ እንዲደርስ ማረጋገጥ፣
- በዱብሊን አገሮች ውስጥ የሚኖርዎትን ቆይታ ለማራዘም በማሰብ በተለያዩ አገሮች ውስጥ ብዙ የጥገኝነት ጥያቄዎችን አለማቅረብዎትን ማረጋገጥ፡፡

የጥገኝነት ማመልከቻዎትን በሀላፊነት የሚመረምረው አገር እስኪወሰን፣ እዚህ ያሉት ሠራተኞች የማመልከቻዎትን ዝርዝር ግምት ውስጥ አያስገቡትም፡፡

ያስታውሱ: ወደ ሌላ የዱብሊን አገር እንዲሄዱ አይጠበቅብዎትም፡፡ ወደ ሌላ የዱብሊን አገር ከሄዱ፣ ወደዚህ ወይም ከዚህ በፊት ጥገኝነት ወደጠየቁበት ቦታ ተመልሰው ይዛወራሉ፡ ፡ ማመልከቻዎትን እዚህ ትዶ መሄድ ሀላፊነት የሚወስደውን አገር አይቀይረውም፡፡ ከተደበቁ ወይም ከሸሹ በቁጥጥር ስር የመዋል አደጋ ይገጥምዎታል፡፡

ከዚህ በፊት በዱብሊን አገሮች በአንዱ ውስጥ ከነበሩ ከዚያም ወደዚህ አገር ከመምጣትዎ በፊት የዱብሊን አገሮች ቀጠናን ለቀው ሄደው ከነበር ሊነግሩን ይገባል፡፡ ይሄም ጠቃሚ የሚሆነው ማመልከቻዎትን ለመመርመር ሀላፊነቱን የሚወስደው አገር የቱ እንደሚሆን



©European Union

ተፅዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ነው። ከዱብሊን አገሮች ውጭ ያሳለፉት ጊዜ ምን ያክል እንደነበር ሊጠየቁ ይችላሉ፣ ለምሳሌ ፓስፖርትዎ ላይ ያለ ማሕተም፣ የመመለስ ወይም የመባረር ውሳኔዎች ወይም ከዱብሊን አገሮች ውጪ መኖርዎን ወይም መስራትዎን የሚያስረዱ ኦፊሲያላዊ ወረቀቶች።

“ሠራተኞቹ ማወቃቸውን ማረጋገጥ የሚኖርብኝ የትኞቹን መረጃዎች ነው?”
“ይሄን መረጃ ለሠራተኞቹ የማብራራው እንዴት ነው?”

የጥገኝነት ጥያቄዎን በሀላፊነት የሚመረምረው የትኛው አገር እንደሆነ ለመወሰን እንዲቻል ቃለ መጠይቅ ሊደረጉ ይችላሉ (የግል ቃለ መጠይቅ)። በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ፣ ‘የዱብሊን አሠራር’ ምን እንደሆነ እናብራራልዎታለን። የቤተሰብ አባል ወይም ማንኛውም አይነት ዘመድ በማንኛውም የዱብሊን አገር ውስጥ ስለመኖሩ ያለዎትን መረጃ በጠቅላላ፣ እዲሁም ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር ለመወሰን ይጠቅማል የሚሉትን ሌላ ማንኛውንም መረጃ ሊሰጡን ይገባል (የትኛው መረጃ ጠቃሚ እንደሆነ ዝርዝር ጥቆማ ከፈለጉ ከዚህ በታች ይመልከቱ) በእጅዎ የሚገኙ ጠቃሚ መረጃ የያዙ ማንኛውም ሰነዶች ወይም ወረቀቶችም ማቅረብ ይኖርብዎታል።

እባክዎን ማመልከቻዎትን ለመመርመር ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር ለመወሰን የሚረዳ ማንኛውም ጠቃሚ መረጃ ሁሉ ይንገሩን።

ቃለ መጠይቁ የሚደረገው እርስዎ በሚረዱት ወይም በምክንያታዊነት ሊረዱት በሚችሉትና ሊግባቡ በሚችሉበት ቋንቋ ይሆናል።

በጥቅም ላይ የሚውለውን ቋንቋ መረዳት ካልቻሉ አስተርጓሚ እንዲኖር መጠየቅ ይችላሉ፡ ፡ አስተርጓሚው እናንተ የምትሉትንና ቃለ መጠይቅ አድራጊው የሚናገረውን ብቻ ይተረጉማል። አስተርጓሚው የራሱን/የራሷን አስተሳሰብ መጨመር የለበትም/የለባትም፡ ፡ አስተርጓሚውን ለመረዳት ችግር ካጋጠመዎ ሊነግሩን ይገባል እና/ወይም ጠበቃዎን ያናግሩ።

ቃለ መጠይቁ በሚስጥር ይያዛል። ይህም ማለት ከሚሰጡት መረጃ ውስጥ የትኛውም መረጃ፣ ለጥገኝነት ማመለከትዎን ጨምሮ፣ የመጡበት አገር ውስጥ የሚገኙ ቤተሰብ አባላትዎ ወይም እርስዎ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ለሚችሉ የመጡበት አገርዎ ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች ወይም ባለ ስልጣናት አይላክም።

ቃለ መጠይቅ የማድረግ መብትዎ የሚከለከሉት ስለ ዱብሊን አሠራርና በእርስዎ ሁኔታ ላይ ስሚያመጣቸው ውጤቶች ከተነገረዎት በኋላ፣ ይሄንን መረጃ በሌላ አይነት ዘዴ ሰጥተው ከሆነ ብቻ ነው። ቃለ መጠይቅ ካልተደረጉ፣ ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር ለመወሰን የሚጠቅም ተጨማሪ መረጃ በጽሑፍ ሊሰጡ ይችላሉ።

“ሠራተኞቹ ማመልከቻዬን ለመመርመር ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር እንዴት ነው የሚወስኑት?” “

አንድ አገር ማመልከቻዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን ሊወስድ የሚችልባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። እነኚህ ምክንያቶች ሕጉ በሰጣቸው ጥቅም የመስጠት ቅደም ተከተል መሠረት ተግባራዊ ይሆናሉ። አንድ ምክንያት ጠቃሚ ባይሆን፣ ቀጣዩ ግምት ውስጥ ይገባል፣ እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

ምክንያቹ ከሚከተሉት ወሳኝ ጉዳዮች ጋር ይገናኛሉ፣ በሚሰጡት ጥቅም ቅደም ተከተል መሠረት፡

- አለም አቀፍ ጥበቃ የተፈቀደለት ወይም በሌላ የዱብሊን አገር ጥገኝነት የጠየቀ የቤተሰብ አባል አለዎት (ባል ወይም ሚስት፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓት በታች የሆኑ ልጆች)
  በዚህም መሠረት በሌላ የዱብሊን አገር ቤተሰብ ካለዎት በጥገኝነት ጥያቄዎት ላይ የመጀመሪያ ውሳኔ ከማለፉ በፊት ለእኛ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። ወደ አንድ አገር በአንድነት እዲመጡ እንዲደረጉ ከፈለጉ እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባል ፍላጎታችሁን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርባችኋል።
- ከዚህ በፊት በሌላ የዱብሊን አገር ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ተሰጥቶዎት ነበር።
- የጣት አሻራዎ በሌላ የዱብሊን አገር ውስጥ ተወስዶ ነበር (እናም ዩሮዳክ በተሰኘው የአውሮፓ የመረጃ ቋት ውስጥ ተቀምጦ ነበር[1])፤
- ምንም እንኳ የጣት አሻራዎ የተወሰደው እዚያ ባይሆንም ወደ ሌላ ዱብሊን አገር፣ ወይም በሌላ ዱብሊን አገር ውስጥ ተጉዘው እንደነበር ማረጃ ከተገኘ።



1) **ስለዩሮዳክ ተጨማሪ መረጃ በዚህ ወረቀት ገጽ 8 ላይ ይገኛል “በአውሮፓ ሕብረት ውስጥ ጥገኝት ጠይቄያለሁ – ጥያቄዬን የሚያየው የትኛው አገር ነው?”**

“ሌላ ሰው ላይ ጥገኛ ብሆን ወይም ሌላ ሰው እኔ ላይ ጥገኛ ቢሆንስ?” “

ከሚከተሉት ውስጥ ሁሉም ሁኔታዎች ከተሟሉ፣ ከ**እናትዎ፣ አባትዎ፣ ልጅዎ፣ ወንድምዎ ወይም እህትዎ** ጋር በአንድ አገር ላይ መልሰው ሊቀላቀሉ ይችላሉ፡፡

- ከዱብሊን አገሮች በአንዱ ውስጥ ሕጋዊ ነዋሪ ከሆኑ፣
- ከሁለት አንዳችሁ እርጉዝ ከሆናችሁ፣ ወይም አዲስ የተወለደ ልጅ ካለ፣ ወይም በጠና ከታመመ፣ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ካለበት ወይም ካረጀ፣
- አንዳችሁ በሌላው ድጋፍ ላይ ጥገኛ ከሆናችሁ፣ እሱ ወይ እሷን ለመንከባከብ የሚችል/የምትችል ከሆነ፡፡

የቤተሰብ ግንኙነታችሁ የነበረው ከመጣችሁበት አገር ጀምሮ ከሆነ፣ በተለምዶ ልጅዎ፣ እህትዎ ወይም ወንድምዎ ወይም ወላጅዎ የሚኖሩበት አገር ማመልከቻዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን ይወስዳል፡፡ ሁሉታችሁም መልሳችሁ መቀላቀል እደምትፈልጉ በጽሑፍ እንድትጠቁሙም ልትጠየቁ ትችላችሁ፡፡

ልጅዎ፣ እህት ወይም ወንድምዎ ወይ ወላጅዎ ባሉበት አገር የሚገኙ ከሆነ ወይም ዘመዶችዎ ከሚኖሩበት በተለየ ቦታ የሚኖሩ ከሆነ ይሄኛውን አማራጭ መጠየቅ ይችላሉ፡ ፡ በዚህ በሁለተኛው አጋጣሚ፣ ለረጅም ጊዜ መጓዝን የሚከለክል የጤና እክል ከሌለብዎት በስተቀር ወደዚያ አገር መጓጓዝ ይኖርብዎታል ማለት ነው፡፡

ከዚህ ሊፈጠር ከሚችል ሁኔታ በተጨማሪ፣ በጥገኝነት ሂደቱ በማንኛውም ጊዜ በሰብዓዊነት፣ በቤተሰብ ወይም ባሕላዊ ምክንያቶች የቤተሰብ ግንኙነትን ለመቀላቀል ሊጠይቁ ይችላሉ፡ ፡ ይህ ተቀባይነት ካገኘ፣ የቤተሰብ ግንኙነትዎ ወደለበት አገር መሄድ ሊኖርብዎት ይችላል፡ ፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ስምምነትዎን በጽሑፍ እንዲሰጡም ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎ እዚህ ወይም በሌላ አገር እንዲመረመር የሚያስደርግ ማንኛውም አይነት ሰብዓዊ ምክንያት ካለ ለእኛ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

የግንኙነት፣ ጥገኝት ወይም ሰብዓዊ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ ሲነሳ ማብራሪያ ወይም አለኝ ስለሚሉት ግንኙነት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

“ብታመም ወይ ልዩ ፍላጎቶች ቢኖሩኝስ?”

ተገቢውን የሕክምና ሽፋን ወይም ሕክምና እንዲያገኙ ስላለዎት ልዩ ፍላጎት እዚህ ያሉት ሠራኞቻችን ማወቅ አለባቸው። ይሄም የእርስዎን ጤና የሚያካትት ሲሆን በተለይም ደግሞ እርስዎ፡

- አካል ጉዳተኛ ከሆኑ፤
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ፤
- አሳሳቢ የጤና እክል ካለብዎት፤
- ግርፋት፣ ተገዶ መደፈር ወይ ሌሎች ከባድ ስነ ልቦናዊ፣ አካላዊ እና ፆታዊ ጥቃት ሰለባ ሆነው ከሆነ፤

የሕክምና ዝርዝርዎን ከነገሩንና ወደ ሌላ አገር እንደሚላኩ ከተወሰነ፣ የሕክምና መረጃዎትን ከሚላኩበት አገር ጋር ለመጋራት ፈቃደኝነትዎን ይጠየቃሉ። በዚህ ካልተስማሙ፣ የሕክምና መረጃውን ከመላክ ያግደዋል፣ ግን ሀላፊነት ወደሚሰጠው አገር መዛወርዎን አያግደውም። የሕክምና መረጃዎን ወደ ሌላኛው አገር እድንልከው ካልፈቀዱ፣ ሌላኛው አገር ልዩ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ እንደማይቻለው ያስተውሉ።

የሕክምና መረጃዎ ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ በገቡ ባለሙያዎች ዘወትር እደሚጠበቅ እባክዎ ያስታውሱ።

“ማመልከቻዬን የሚቀበለው የትኛው አገር እደሆነ ለመወሰን ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? ማመልከቻዬ ከመመርመሩ በፊት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?”

እዚህ አገር ያሉት ሠራተኞች የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ ለመመርር ሀላፊነቱን የምወስደው እኛ መሆናችን ከወሰኑ፣ እዚህ አገር ቆይተው ማመልከቻዎን እዚህ ማስመርመር ይችላሉ ማለት ነው።

“ማመልከቻዬን ለመመርመር አሁን ካለሁበት የተለየ ሌላ አገር ሀላፊ ሆኖ ቢገኝ ምን ይፈጠራል? ”

ማመልከቻዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን የሚወስደው ሌላ አገር ነው ብለን ግምት ከወሰድን፣ ማመልከቻዎን ለዚህ አገር ካስረከቡበት ቀን ጀምሮ በ **3 ወራት** ጊዜ ውስጥ ያ አገር ሀላፊነቱን እንዲወስድ እንጠይቃለን።

ሆኖም፣ የሌላ አገር ሀላፊነት የተወሰነው የጣት አሻራዎን መረጃ መሠረት አድርጎ ከሆነ፣ ለሌላ አገር የቀረበው ጥያቄ በ **2 ወራት ጊዜ ውስጥ ይላካል** ውጤቶቹ ከዩሮዳክ ከተገኙበት ቅጽበት ጀምሮ።

- በዱብሊን አገር ለጥገኝነት ሲያመለክቱ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዎት ከሆነ ሆኖም የጥገኝነት ጥያቄዎ በሌላ የዱብሊን አገር እንዲመረመር ምክንያትት ሲኖር፣ ያኛው አገር የእርስዎን ጉዳይ እንዲወስድ እንጠይቃለን።

ጥያቄውን የምናቀርብለት አገር ጥያቄው በቀረበለት **በ2 ወራት** ውስጥ መልስ መስጠት አለበት። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ያ አገር መልስ ካልሰጠ፣ የማመልከቻዎን ሀላፊነት ወስዷል ማለት ነው።

- አሁን ካሉበት በተለየ የዱብሊን አገር የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተው ከሆነ፣ ያ አገር መልሶ እንዲዎስድዎ እንጠይቃለን።

ጥያቄው የሚቀርብለት አገር ጥያቄውን በተቀበለ በ **1 ወር** ውስጥ ወይም ጥያቄው በዩሮዳክ መረጃ የተመሠረተ ከሆነ በ **2 ሳምንት** ውስጥ መልስ መስጠት አለበት። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ያ አገር መልስ ካልሰጠ፣ የማመልከቻዎን ሀላፊነት ወስዷል፣ መልሶ ሊወስድዎትም ተስማምቷል ማለት ነው።

ሆኖም ግን፣ እዚህ አገር ላይ የጥገኝነት ጥያቄ ካላቀረቡና ከዚህ በፊት በሌላ አገር ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ በመጨረሻ ውሳኔ ውድቅ ከተደረገ፣ መልሰው እንዲወስዱዎት ሀላፊነቱን የሚወስደውን አገር መጠየቅን ልንመርጥ ወይም ወደመጡበት አገር ልንመልስዎ ወይም ወደ ቋሚ መኖሪያዎ ወይም ምቹ ወደሆነ ሦስተኛ አገር ልንልክዎ እችላለን።

ማመልከቻዎን ለመመርር ሌላ አገር ሀላፊነቴ ነው ካለ፣ ውሳኔያችንን አስመልክቶ መረጃ ይሰጥዎታል፡

- እዚህ አገር ላይ የጥገኝነት ጥያቄዎትን ላለመመርመርና፣
- ሀላፊነቱን ወደሚወስደው አገር እርስዎን ለማዛወር፡፡

እርስዎን የማዛወሩ ስራ ሌላኛው አገር ሀላፊነቱን ከወሰደ በ6 ወራ ጊዜ ውስጥ ወይም በውሳኔው አልስማማም ካሉ ፍርድ ቤት ወይም ሸንጎ ወደዚያ አገር መሄድ እንደሚኖርብዎት በወሰነ በ6 ወራት ውስጥ ይከናወናል፡፡ ከሚለከተው አካል ከሸሹ ወይም እስር ቤት ከገቡ ይህ የጊዜ ገድብ ሊራዘም ይችላል፡፡

በማረፊያ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ከተደረገ/ በዱብሊን አሠራር መሠረት የተዘጋበት ማዕከል፣ አጫጭር የጊዜ ገደቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ (ለበለጠ መረጃ በማረፊያ ቤት ስለመቆየት በዝርዝር የሚያሳየውን ክፍል ይመልከቱ)

ሀላፊነቱን የሚወስደው አገር የሚይዝዎት እንደ አንድ ጥገኝነት ጠያቂ ሲሆን ሁሉንም ተያያዥ የሆኑ መብቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በዚያ አገር ከዚያ በፊት የጥገኝነት ጥያቄ አላቀረቡ ከሆነ እዚያ ከደረሱ በኋላ ለማመልከት ዕድሉ ይሰጥዎታል፡፡

“ወደ ሌላ አገር እንድዛወር በተወሰነው ላይ ባልስማማስ?”

ወደ ሌላ የዱብሊን አገር እንዲሄዱ በተወሰነው ላይ ያለመስማማትዎን ለመግለጽ ዕድሉ ሊኖርዎት ይችላል። ይህም 'ይግባኝ' ወይም 'ክለሳ' ይባላል። በይግባኝ ወይም ክለሳ ወቅት ማዛወሩ እንዲቆይ መጠየቅም ይችላሉ።

እዚህ አገር ላይ ያለፈውን ውሳኔ ለመቃወም የትኞቹን ሠራተኞች ማናገር እንደሚኖርብዎት መረጃ በዚህ ወረቀት መጨረሻ ላይ ሊያገኙ ይችላሉ።

የማዛወር ውሳኔውን ከሠራተኞቹ ስትቀበሉ፣ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት 21 ቀናት አላችሁ። ለመቃወም (ይግባኝ ወይም ክለሳ) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው።

ይግባኝዎት እየታየ እያለ መዛወርዎ እንዲቆይ ለመጠየቅ ሰባት (ቀናት) አለዎት። ፍድ ቤት ወይም ሸንጎ በዚህ ጥያቄ ላይ ውሳኔውን በፍጥነት ያሳልፋል። የማቆየት ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ፣ ለምን እንደዚያ እንደተደረገ ምክንያት ይሰጥዎታል።

በዚህ ሂደት ውስጥ የሕግ ድጋፍ የማግኘት አስፈላጊ ከሆነም የቋንቋ ድጋፍ የማግኘት መብት አለዎት። የህግ ድጋፍ ማለት ወረቀቶችዎን የሚያዘጋጅና ፍርድ ቤት ውስጥ እርስዎን የሚወክል ጠበቃ ይኖርዎታል ማለት ነው።

ዋጋውን መሸፈን ካልቻሉ ይህ አገልግሎት በነጻ እንዲሰጥዎ መጠይቅ ይኖርብዎታል። የሕግ ድጋፍ ስለሚሰጡ ድርጅቶች መረጃ በዚህ ወረቀት መጨረሻ ላይ ይገኛል።



©iStockphoto / Joe Gough

“ማረፊያ ቤት ውስጥ እንድቆይ ሊደረግ ይችላል? “

ማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረግባቸው ሌሎች ምክንያቶች ይኖራሉ፣ ለዱብሊን አሠራር ሲባል ግን ማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረገው ወደ ሌላ የዱብሊን አገር መላክ ስለማይፈልጉ ሊሸሹ ይችላሉ ተብሎ በሠራተኞቻችን ግምት ከተወሰደ ብቻ ነው።

“ይህ ምን ማለት ነው? “

እርስዎ ከእኛ ሊሸሹ የሚችሉበት ሰፊ ዕድል እንዳለ ሠራተኞቻችን ካመኑ -- ለምሳሌ ከዚህ በፊትም እደዚህ አድርገው የሚያውቁ ከሆነ ወይም ግዴታዎችዎን ሪፖርት በማድረግ ካልተስማሙ ወዘተ... -- በዱብሊን አሠራር ወቅት በማንኛውም ሰዓት ማረፊያ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ሊያደርጉዎት ይችላሉ። ማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረጉባቸው ምክንያቶች በሕግ ተጽፈዋል። በሕግ ውስጥ ካሉት ምክንያቶች ውጭ እርስዎን በማረፊያ ቤት ለማቆየት ጥቅም ላይ አይውሉም።

ለምን በማረፊያ ቤት ውስጥ እዲቆዩ እደተደረገ እንዲሁም በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ የተላፈውን ትዕዛዝ መቃወም ስለሚችሉበት ሁኔታ በጽሑፍ የማግኘት መብት አለዎት፡ ፡ በማረፊያ ቤት እንዲያርፉ የተላፈውን ውሳኔ የመቃወም ፍላጎት ካለዎት የሕግ ድጋፍ የማግኘት መብት አለዎት።

በዱብሊን አሠራር ወቅት ማረፊያ ቤት እዲቆዩ ከተደረገ፣ ለአሠራሩ የሚቀመጥልዎት የጊዜ ገደብ የሚከተለው ይሆናል፡

- ሌላኛው አገር የጥገኝነት ማመልከቻዎን ባስገቡ በ1 **ወር** ውስጥ ሀላፊነቱን እንዲረከብ እንጠይቃለን።
- ጥያቄውን የምናቀርብለት አገር ጥያቄውን በተቀበለ በ2 **ሳምንታት** ውስጥ መልስ መስጠት አለበት።
- ዝውውርዎ ሀላፊነቱን የሚወስደው አገር ጥያቄውን በተቀበለ በ6 **ሳምንታት** ውስጥ መደረግ ይኖርበታል። የማዘዋወሩን ውሳኔ ከተቃወሙ፣ 6ቱ ሳምንታት የሚቆጠሩት ሠራተኞቹ ወይም ፍርድ ቤት ወይም ሸንጎ ይግባኝዎ እየታየ እያለ ወደሌላ አገር መላክዎ ምቹ መሆኑን ከወሰኑበት ጊዜ ጀምሮ ይቆጠራል።

ጥያቄውን ለመላክ ወይም ዝውውርዎን ለማድረግ ካልቻልን በዱብሊን ድንጋጌ መሠረት እርስዎን ለማዛወር አላማ በማረፊያ ቤት መቆየትዎ ያበቃል። እንደዚያ ከሆነ ከላይ የተቀመጡት የተለመዱት የጊዜ ገደቦች ተግባራዊ ይሆናሉ።

“የምሰጠው የግል መረጃ ምን ይሆናል? ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንደማይውል እንዴት አውቃለሁ?”

በዱብሊን አሠራር ወቅት፣ በዱብሊን እና ዩሮዳክ ድንጋጎች ስር ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት ጉዳይ ብቻ፣ የዱብሊን አገሮች ሠራተኞች እርስዎ የሚሰጡትን መረጃ መጋራት ይችላሉ። በዱብሊን አሠራ ወቅት ሁሉም የግለሰብ ዝርዝሮችዎ እና ስለራስዎ፣ ስለ ቤተሰብዎ ሁኔታ ወዘተ የሚሰጡት መረጃ ጥበቃ እንዲደረግለት የማድረግ መብት አለዎት። መረጃዎት ጥቅም ላይ የሚውለው በሕግ ለተቀመጡት አገልግሎቶች ብቻ ነው።

ክፍት እንዲሆንልዎ መብት የሚኖርዎት፡

- ከእርስዎ ጋር ተያያዥ ለሆነ መረጃ። እንዲህ አይነቱን መረጃ ትክክል ካልሆነ ሊስተካል የሚገባው የዩሮዳክ መረጃን ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋሉ እዲሰረዙ ጭምር የመጠየቅ መብት አለዎት።
- የዩሮዳክ መረጃዎትን ጨምሮ መረጃዎችዎት መስተካላቸውን ወይም መሰረዛቸውን ስለመጠየቅ የሚያብራራው መረጃ። ይሄም ለእርስዎ የዱብሊን አሠራር ሀላፊነቱን የሚወስዱ ብቁ ባለሙያዎችን እና የግል መረጃ ጥበቃን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚያስተናግዱ የብሔራዊ የመረጃ ጥበቃ ሠራኞችን ያካትታል።





1.9.2016 amhara